# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1996 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም
## ግምገማ ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1996

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1996 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1996

# ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ | 3 |
| 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | 3 |
| 2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት | 7 |
| 2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት | 11 |
| 2.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት | 13 |
| 3. ሳምፕሊኒንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ | 14 |
| 4. የመረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ | 18 |
| 5. የአካባቢ ጽ/ቤቶችና የመስክ ሥራ ክንውንን በተመለከተ | 19 |
| 6. የ1996 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም | 22 |
| 7. የ1995 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ | 24 |
| 8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ዝግጅትን በተመለከተ | 24 |
| 9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት | 27 |
| 10. የኦዲት አገልግሎት | 29 |
| 11. የሕግ አገልግሎት | 30 |
| 12. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት | 30 |
| 13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት | 31 |
| 12.1 የሰው ኃይል ሁኔታ | 31 |
| 12.2 የበጀት አጠቃቀም | 32 |
| 12.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ጉዳዮች | 35 |
| 14. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች | 38 |

# የ1996 በጀት ዓመት
# የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከመንግስት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር መሠረት በማድረግ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሱ ጥናቶችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ መ/ቤቱ በተለያዩ ዘርፎች ያለውን የአገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት ለማሟላትና የመረጃ ክፍተቱን ለማጥበብ በየዓመቱ በመንግሥትና በረጂ ድርጅቶች ከሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ በርካታ ጥናቶችን በማካሄድ ላይ ነው፡፡

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ባለፉት ዓመታት ያካሄዳቸው ስታቲስቲካዊ ጥናቶች ለመንግስትና ለሌሎች መረጃ ተጠቃሚዎች ለተለያዩ ሥራዎች፣ ዕቅዶችና ምርምሮች መነሻ በመሆን ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን፤ አሁንም ይህንን አገልግሎትና ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የሚያስገኙ ጥናቶችን ለማካሄድ በርካታ ዕቅዶች ለ1996 በጀት ዓመት ተይዘው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በዚሁም መሠረት በ1996 በተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም ስር በርካታ ጥናቶችን ለማከናወን፣ ከ1995 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብና ማጠናቀር ሥራዎቻቸው ያለቀላቸውን ጥናቶች ሪፖርት ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ዝርዝር የአፈፃፀም ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥናቶች ማለትም፡-

ሀ/ <u>በ1995 በጀት ዓመት የተጀመሩና በ1996 የተጠናቀቁ ጥናቶች</u>

- የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ
  - የ1994 ግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ስራዎች
- የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ
  - የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል መከራ ጥናት
- የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ
  - የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት
  - የጎጆ/ ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት
  - የመደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት
  - የአከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥናትና
  - የ1994 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

ለ/ በ1996 በጀት ዓመት የተከናወኑ አዳዲስ ጥናቶች

- የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ
  - የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /በገጠር/
  - የሰብል ምርት ጥናት በመኸርና በበልግ /በገጠር/
  - የመሬት አጠቃቀም ጥናት /በገጠር/
  - የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት /በገጠር/
  - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት /በገጠር/
  - የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት /በገጠር/
  - በሱማሌና በአፋር ክልሎች የቤት እንስሳት ቆጠራ
- የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ
  - የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በከተማ/
  - የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ
- የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ
  - የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
  - የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት /በተመረጡ ገበያዎች/
- የማኅበራዊ ስታቲስቲክስ
  - ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት /በከተማ/ Current Employment survey/
- ከአስተዳደር መዛግብት የሚዘጋጁ የስታቲስቲክስ ሪፖርቶች
  - የኤሌትሪክ ኢንዱስትሪ ጥናት
  - የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ
  - ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት በየዘርፉ የተሰበሰቡ መረጃዎች
- በዕቅድ ከተያዘው ውጪ በመንግስትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥያቄ የተከናወኑ፣
  - የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት
  - የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት

በዕቅድ በመያዝ የመረጃ መሰብሰብ፣ ማጠናቀርና ሪፖርት የማዘጋጀት ተግባር እያከናወነ ይገኛል፡፡

በዚህ ሪፖርት ዉስጥ ከላይ የተጠቀሱትን ጥናቶች ለማካሄድ በበጀት ዓመቱ በመ/ቤቱ የተደረገዉ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ለማካተት የተሞከረ ሲሆን፤

ከዚህም ጋር የመ/ቤቱ የሰዉ ኃይል ሁኔታ፣ የበጀት አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራትን የሚያሣዩ አኃዛዊ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና ለቀጣዩ በጀት ዓመት የበላይ አካልን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 2. የኢኮኖሚ ስታቲስቲክስ

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

#### 2.1.1 የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- ለ1996 ዓ.ም በሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በተሻለ ፍጥነት ከመስክ ሰብስቦና የቅንብሩ ሥራም ቀደም ካሉት ዓመታት አጠር ባለ ጊዜ ተጠናቆ ሪፖርት ለተጠቃሚዎች የሚደርስበትን ሁኔታ ሊያመቻች የሚችል የአሰራር ሥርዓት በተግባር እንዲተረጐም ተደርጐ ከምንግዜውም በተሻለ ፍጥነት የመረጃው ውጤት ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

- በወረዳ ደረጃ ለ1996 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ (Early Forecast) ጥናት የሚያገለግል መጠይቅና መመሪያ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲዉል ተደርጓል፡፡ ለዚህም ጥናት የሚያገለግል በመስክ ደረጃ ኤዲትና ኮድ ማድረጊያ መመሪያም ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ዉሏል፡፡ እንዲሁም ለ1996 ዓ.ም ለዋናዉ መኸር ምርትን ለመተንበይ የሚያስችሉ በወረዳ ደረጃ ከየቅ/ጽ/ቤቶቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች በባለሙያዎች በማጠናቀር ሥራው ተጠናቆ የሪፖርት ዝግጅቱ ከወጣዉ መርሃ-ግብር ቀደም ብሎ ተከናውኗል፡፡

#### 2.1.2 የእርሻ መሬት ስፋትና የሰብል ምርት መጠን ጥናት መረጃን በተመለከተ

- ለ1996 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ የመጠይቆችና መመሪያዎች ዝግጅት ተጠናቆ በሥራ ላይ እንዲዉል ተደርጓል፡፡

- የ1996 ዓ.ም ዋናው መኸር ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን መረጃ ውጤት ቅንብር ተጠናቆ፣ መረጃው ተገምግሞና ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- በ1997 በጀት ዓመት ለሚካሄደው የቋሚ ሰብሎች፣ ለአትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች መስራ ጥናት የሚያገለግሉ የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅት ተጠናቋል::

#### 2.1.3 የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን መረጃን በተመለከተ

ለ1996 የዋናው መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃው ከመስክ ተሰብስቦ፣ ተቀነባብሮና የሪፖርት ዝግጅት ሥራው ተጠናቆ ለህትመት ተጠናቋል::

#### 2.1.4 የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ

ለ1996 ዓ.ም መኸር ወቅት የመሬት አጠቃቀም መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ የቅንብር ሥራው በኮምፒውተር ተከናውኖ የሪፖርት ዝግጅቱ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

#### 2.1.5 የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ

- ለ1996 ዓ.ም የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሃብትን ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃን ለመሰብሰብ የሚረዱ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል::

- የ1996 ዓ.ም የቤት እንስሳት መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የመረጃ ቅንብር ሥራዎች በኮምፒውተር ተሰርተው ሪፖርቶች ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

#### 2.1.6 የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ ሪፖርት ዝግጅትና ቀሪ ሥራዎችን በተመለከተ

- የግብርና ናሙና ቆጠራ ዉጤት የሆኑት የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሐረሪ፣ የጋምቤላ፣ የአፋር፣ የሱማሌ፣ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ መስተዳድርና የድሬደዋ ካውንስል ሪፖርት ምዕራፎች ትንተና ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

- በተጨማሪም የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው የአገር አቀፍ በሰብል የተያዘ መሬት ስፋት ምርታማነት በሄክታር የሰብል

አጠቃቀም የሚያመለክት ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነዉ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች የሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ የጽሁፍ ሥራዎችና በኮምፒውተር የማቀነባበሩ ተግባር ተጠናቆ የመረጃዎቹ የእርስ በርስ መጣጣምና አስተማማኝነት ተገምግሞ የዋናው ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቋል።

- የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ የእርሻ መሳሪያዎችና ማከማቻዎች የግብርና ቤተሰቦች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያት እንዲሁም መሰል መረጃዎች በየክልሎቹ በሚወጡት ስታቲስቲካዊ ሪፖርቶች ተካተው እንዲዘጋጁ ተደርጓል።

- የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነዉ የአርብቶ አደሩ አካባቢ በአፋርና በሱማሌ ክልል ለተካሄደው የቤት እንስሳት ቆጠራ የሚያገለግሉ መጠይቆችና የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል።

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ የሐረሪ፣ የጋምቤላ ክልሎችና የአዲስ አበባ መስተዳድር እንዲሁም የድሬደዋ ካውንስል የቤት እንስሳት መረጃዎች የሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። በተጨማሪም የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው የአገር አቀፍ የቤት እንስሳት መረጃ የያዘው ሪፖርት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- በሱማሌ ብሔራዊ ክልል ዝቅ ብሎ በሚበር አዉሮፕላን ለተካሄደዉን የቤት እንስሳት ቆጠራ አጋዥ ሊሆን የሚችል መደበኛ የአቆጣጠር ሥርዓትን የተከተለዉ የ Ground truthing መረጃ ተሰብስቦና ተቀናብሮ ዉጤቱ ለበላይ አካልና በአዉሮፕላን ቆጠራዉን ላካሄደዉ ኩባንያ Ecosystem Consultants ተልኳል።

- በሌላ በኩል በአዉሮፕላን ቆጠራ ያልተሸፈኑትን ቀሪ የሱማሌ 3 ወረዳዎች በባቢሌ፣ በጉርሱምና በሐርሺን የቤት እንስሳት ቆጠራው

በኮንቬንሽናል ዘዴ በመጠቀም መረጃ የመሰብሰብ ሥራ ተከናውኖ ውጤቱ በክልሉ በተዘጋጀው የቆጠራ ሪፖርት ላይ እንዲካተት ተደርጓል።

- በአፋርና ሱማሌ ብሔራዊ ክልሎች የተከናወነው የቤት እንስሳት ቆጠራ ውጤትና የ1996 ግብርና ናሙና ጥናት የቤት እንስሳት የመረጃ በአንድ ላይ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤትን ለመረጃ ተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅ ግንቦት 12/1996 ዓ.ም የፌደራልና የክልል የዘርፉ ባለሙያዎች በተገኙበት የአንድ ቀን አውደ ጥናት ተካሂዷል።

- የ1994 ዓ.ም ግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆኑት የኦሮሚያ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና የሐረሪ፣ የጋምቤላ የአፋር፣ የሶማሌ ክልል፣ የአዲስ አበባ መስተዳድርና የድሬደዋ ካውንስል የመሬት አጠቃቀም መረጃ የያዙ የሪፖርት ምዕራፎች የትንተና ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል። እንዲሁም የ1994 አካል የሆነው የአገር አቀፍ የግብርና ናሙና የመሬት አጠቃቀም መረጃ የያዙ የሪፖርት ምዕራፍ ትንተና ዝግጅት ተጠናቆና መረጃው ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

### 2.1.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ስ1996 ዓ.ም በበልግ ወቅት ለጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆች ተዘጋጅተውና ታትመው ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሰራጩ ተደርጐ የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ተከናውኗል።

- በተመሣሣይ በ1996 ዓ.ም መ/ቤቱ ለሚያካሄደው የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆችን፣ የአሞላልና የቁጥጥር መመሪያዎችን አዘጋጅቶ እንዲታተሙ በማድረግ በመስክ የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል።

- በዘርፉ ከተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለሚቀርቡ መረጃ ጠያቂዎች አስፈላጊው አገልግሎት ተሰጥቷል።

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀዉ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ መረጃዎች ተሰብስበዉና የትንተና ሥራቸው ተከናውኖ ውጤቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

- በ1997 ዓ.ም ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ጥናትና የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት እንዲሁም ለሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆች ተዘጋጅተው ለህትመት የቀረቡ ሲሆን የመረጃ ሰብሳቢዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያ ዝግጅትም በመገባደድ ላይ ነው፡፡

**2.2** <u>የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

**2.2.1** <u>የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶች ዝግጅትን በተመለከተ</u>

ሀ. <u>በገጠር የግብርና ዉጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት</u>

- ለ1996 የሚያገለግሉ የዋጋ ጥናት መጠይቆች ታትመዉ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- የ1995 ዓ.ም አጠቃላይ የዓመቱን መረጃ የያዘዉ የአምራቾች ዋጋ ጥናት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- ከሐምሌ ወር 1995 ዓ.ም እስከ የካቲት ወር 1996 ዓ.ም ድረስ ያለዉ ወርሃዊ የአምራቾች ዋጋ መረጃ ተቀነባብሮና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን፤ የመጋቢት ወር 1996 ዓ.ም ተቀነባብሮ ለሕትመት ተልኳል፡፡ እንዲሁም የሚያዝያ ወር 1996 መረጃ ደግሞ በመቀነባበር ላይ ይገኛል፡፡

- የአምራቾች ዋጋ ጥናት ሪፖርት የየሦስት ወሩ በአንድ መጽሔት የሚታታም በመሆኑ ተጠቃሚዎች ሕትመቱ እስኪደርስ እንዳይጉላሉ መረጃዉ ከተጠናቀረ በኋላ ሪፖርቱን ከቤተመጽሐፍት እንዲያገኙት የተወሰኑ ቅጂዎች እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም አገልግሎቱን የበለጠ ለማሻሻል ሪፖርቱ በየወሩ ታትሞ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

ለ. ወርሃዊ የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

- ለ1996 በጀት ዓመት የሚያገለግል መጠይቅ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ተደርጓል።

- የ1995 በጀት ዓመት መረጃ ተቀነባብሮና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- ከሐምሌ ወር 1995 ዓ.ም እስከ መጋቢት ወር 1996 ዓ.ም ድረስ ያለዉ መረጃ ተቀነባብሮና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጀዉ የሆቴሎች ዋጋ መረጃም ከመስከረምና ከታህሳስ ሪፖርት ጋር ተጠቃሎ ወጥቷል። እንዲሁም ከሚያዝያ ወር እስከ ግንቦት ወር 1996 ዓ.ም ያለው መረጃ ተቀነባብሮ ለሕትመት ተልኳል። በተጨማሪም የሰኔ ወር 1996 ዓ.ም መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

### 2.2.2 <u>ወርሃዊ የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ</u>

ሀ. <u>የሀገር አቀፍና የክልሎች የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ</u>

- የሀገር አቀፍና የክልሎች የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዞች እስከ ሰኔ ወር 1996 ዓ.ም ድረስ ያለዉ መረጃ በየወሩ ታትሞ በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

ለ. <u>የአዲስ አበባ ከተማ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ አኃዝ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አኃዝ እስከ ሰኔ ወር 1996 ዓ.ም ድረስ ያለዉ መረጃ በየወሩ ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

### 2.2.3 <u>የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት</u>

- ይህ ጥናት እ.ኤ.አ ከ1995/96 ጀምሮ እየተከናወነ ካለዉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት Welfare Monitoring Survey (WMS) ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የሚለየዉ በአሠራሩ እንዲሁም በይዘቱ አነስ ያለና የተጨመቀ በመሆኑ ነዉ። አሠራሩም የጥናቱን ዉጤት በፍጥነት

ለማጠናቀቅ እንዲያስችል ተደርጎ የተነደፈ ነዉ። ዋናዉን ጥናት ለመተግበር የሚያስችል የሙከራ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ በመሆኑ የሙከራ ጥናቱ በአራት ወረዳዎች ተከናዉኗል። የሙከራ ጥናቱም የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት አሠራርን ለመገምገም በሚያስችል መልኩ የተከናወነ ሲሆን የሚከተሉት ተግባራት ተከናዉነዋል።

- የመረጃ መሰብሰብ ተግባር በሐምሌ ወር 1995 ተጠናቋል።
- ስልጠና በሐምሌ ወር 1995 ተካሂዷል።
- የዳታ ኢንትሪና የስካኒንግ ሥራዎች ተጠናቀዉ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።
- የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት አሠራርን ለመገምገም የሚረዳ ትንተና በመከናወን ላይ ይገኛል።
- ለሙከራ የተመረጡ አራት ወረዳዎች ሪፖርት በመጠናቀር ላይ ይገኛል።

### 2.2.4 <u>የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት እና የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናትን በተመለከተ</u>

- ለድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ክትትል አስፈላጊ የሆኑትን የቤተሰብ ኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት እና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት ትግበራ የሚያስፈልጉ ዶክመንቶች፣ መጠይቆች፣ የመረጃ አሰባሰብ መመሪያዎች......ወዘተ የፍተሻ ሥራ በአዲስ አበባ ከተማና በዱከም አካባቢ እንዲከናወን ተደርጓል።

- የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎትና አስተያየት ለማካተት እንዲቻል መጠይቁ ለበርካታ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ተሰራጭቶና የአንድ ቀን ሴሚናር ተካሄዶ ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት መሰረት መጠይቁ እንዲሻሻልና ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- በ1996 ዓ.ም ለተካሄደው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት ከመላው አገሪቱ ናሙና በተመረጡ 2862 ቆጠራ ቦታዎች ላይ በተዘጋጀው መጠይቅ፣ የአሞላልና የቁጥጥር መመሪያ መሰረት ከሰኔ

15 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 27 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ መረጃ ተሰብስቦ ከሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ ዋናው መ/ቤት ተልኳል፡፡

- በተመሣሣይ የመጀመሪያው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ከመላው አገሪቱ በተመረጡ 1620 የቆጠራ ቦታዎች ላይ በተዘጋጀው መጠይቅ፣ የአሞላልና የቁጥጥር መመሪያ ከሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ መሠረት ከመስክ መረጃ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል፡፡

2.2.5 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀዉ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ መረጃዎች ከየድርጅቶቹ ተሰብስበዉና ተጠናቅረዉ ለሚመለከተዉ ክፍል ተላልፏል፡፡

- የዋጋ ጥናቶችን አስመልክቶ ያለዉ የዓመቱ መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸዉ የሥራ ክፍሎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- የተሳትፏዊ የድህነት ዳሰሳ ጥናት (Participatory Poverty Assessment - PPA) ፕሮፖዛልና በጀት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴት ስር ከሚገኘው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ዕቅድ መምሪያ ጋር በመሆን ተሰርቷል፡፡

- የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት እንዲሁም መ/ቤቱ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ሊያካሂድ ላቀዳቸዉ ጥናቶች የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ለለጋሽ ድርጅቶች ቀደም ብሎ በተዘጋጀዉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ላይ በለጋሽ ድርጅቶቹ ከተቀጠሩት አማካሪ ጋር በመሆን የተሰራዉ ዶክመንት በአማካሪዉ ተጠቃሎ በመ/ቤቱ ለመጨረሻ ጊዜ ከታየ በኋላ ክለሳዉ ተጠናቋል፡፡ ይህን ሰነድ ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር የፊርማ ሥነ-ሥርዓት ተከናውኖ ፋይናንሱ ገቢ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

## 2.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት

### 2.3.1 የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶችን በተመለከተ

#### ሀ. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ጥናት

- በ1995 በሚያዚያና ግንቦት ወራት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1994 ዓ.ም የሚመለከት የዘርፉ ጥናት የመረጃ ቅንብርና ትንተና ሥራ ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- የ1995 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የዘርፉን ጥናት መረጃ የመሰብሰብ ሥራ ተጠናቆ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

#### ለ. የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃን በተመለከተ

የዘርፉ የ1994 ዓ.ም የሚመለከት መረጃ የሠንጠረዥ ቅንብርና ትንተና ሥራ ተካሂዶና ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

#### ሐ. የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትን በተመለከተ

በ1995 ዓ.ም ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመረጃ ቅንብርና ትንተና ሥራ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

#### መ. የጎጆ/ ዕደ ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትን በተመለከተ

በ1995 ዓ.ም ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት መረጃ ቅንብርና ትንተና ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደረጓል፡፡

#### ሠ. የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራን በተመለከተ

በ1996 የዕቅድ ዘመን በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ/ምዝገባ የሚያገለግሉ

የመጠይቆችና የአሞላል መመሪያዎች ከመዘጋጀታቸውም በላይ የመረጃ መሰብሰቡ ሥራ ተጠናቆ በአሁኑ ወቅት የኤዲቲንግ፣ኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

### 2.3.2 የንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

#### ሀ. የአከፋፋይና አገልግሎት ሰጭ ንግድ ጥናትን በተመለከተ

በ1995 ዓ.ም በጀት ዓመት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የዘርፉ ጥናት መረጃ ቅንብር ትንተናና ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

#### ለ መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናትን በተመለከተ

በ1995 በጀት ዓመት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ የተጠናቀቀለት መደበኛ ያልሆነ የሥራ የዘርፉ ጥናት /Informal sector/ የመረጃ ቅንብርና ትንተና ተግባር ተከናውኖና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

#### ሐ. የውጭ ንግድና መረጃን በሚመለከት

እ.ኤ.አ የ2003 እና እንደዚሁም የ2004 የዘመኑ የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ ሙሉ በሙሉ ተሰብስቦ የመረጃ ቅንብር ሥራዉ ተጠናቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

#### መ. የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃን በተመለከተ

የ1995 ዓ.ም የዘርፉ መረጃ ተሰብስቦ፣ ተቀናብሮና ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

### 2.3.3 ሌሎች ሥራዎችን በተመለከተ

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀዉ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚያገለግሉ ዘርፉን የተመለከቱ የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበዉና ተጠናቅረዉ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡

- በ1997 ዓ.ም ለሚካሄዱ የወቅታዊ የማምረቻ ንግድና የአገልግሎት ጥናትና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርትና የዋጋ ጥናት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

- በሁሉም ዘርፎች ለመረጃ ተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠትና አጠቃቀሙን የማስረዳት ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 2.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

### 2.4.1 የሰዉ ኃይል ስታቲስቲክስ

- በከተሞች ወቅታዊ የሥራ ስምሪት አንደኛ ዙር ጥናትን በሚመለከት የመጠይቅና የአሞላል መመሪያዎች ተዘጋጅተው መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበው የመረጃ ዕርማት፣ኮዲንግ፣ የክሊኒንገ ሥራ ተከናውኖ የጥናቱ ሪፖርት ተጠናቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- ለሁለተኛው ዙር ወቅታዊ የሥራ ስምሪት ጥናት በተመለከተ መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበው የማንዋል የኤዲቲንግ ሥራ ተጠናቆ የቬሪፊኬሽን ሥራም የተገባደደ ሲሆን መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

### 2.4.2 የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ

- የህግና ደንብ ስታቲስቲክስን በሚመለከት መረጃዎች ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተሰብስበው፣ መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት እንዲውሉ ተጠናቅረውና የሠንጠረዥ ሥራው ተጠናቆ ለሚመለከታቸው ክፍል ተልኳል፡፡

- የ Care and Support እና የማህበራት መረጃዎችን መረጃ አመንጭ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር በመነጋገር የ2ኛ ደረጃ ምንጭ የሚሆኑ መ/ቤቶች ተለይተው መረጃዎች የሚሰበሰቡበት የመጠይቅ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

### 2.4.3 የትምህርት፣ ባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስ

- ዘርፉን በተመለከተ መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀዉ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበዉና የሠንጠረዥ ስራው አልቆ ለሚመለከተዉ ክፍል ተላልፏል።

- የባህል መረጃን በሚመለከት ከመረጃ አመንጭ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መጠይቆችና ቅጾች ተዘጋጅተው የሙከራ መረጃዎች በመሰባሰብ ላይ ናቸው።

- በአገር አቀፍ ደረጃ በመካሄድ ላይ ለሚገኘው የወረዳ ኔት አስፈላጊው ዝግጅት በመካሄድ ላይ ይገኛል።

### 2.4.4 <u>የጤና ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀዉ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ ጤና ነክ መረጃዎች ተሰብስበዉና ተጠናቅረዉ ለሚመለከተዉ ክፍል ተላልፈዋል።

### 2.4.5 <u>ሌሎች ሥራዎችን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በ Gender ጉዳይ በአገር አቀፍ ደረጃ በተቋቋመው ኮሚቴ ጋር የተለያዩ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

## 3. <u>ሣምፕሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ</u>

- ለ1996 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት የሚሸፈኑ 2072 የቆጠራ ቦታዎች ናሙና ምርጫ የተካሄደ ሲሆን፣ የናሙናዉ ምርጫ ዝርዝር የያዘ ኮድ በኑክም ተዘጋጅቶና ታትሞ ለሚመለከታቸዉ ክፍሎች ተሰጥቷል። እንዲሁም የአካባቢ መለያን መስክ ላይ ለመሙላት የሚያገለግል የናሙና ቆጠራ ቦታ ዝርዝር ኮድ በየቅ/ጽ/ቤት ተዘጋጅቶ ለ25ቱም ጽ/ቤቶች ተሰራጭቷል።

- የቤተሰቦች አመዘጋገብ፣ አመራረጥና የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ በግብርና ናሙና ጥናት ሥልጠና ወቅት ለአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- በጥቅምት ወር 1996 ዓ.ም ለተካሄደዉ የከተሞች ወቅታዊ የሥራ ስምሪት 1ኛ ዙር ጥናት የሚያገለግል ሳምፕሊንግ ሜቶዶሎጂ ተዘጋጅቶ በ99 ከተሞች ዉስጥ ባሉ የ527 የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ምርጫ ተካሂዶ የናሙናዎቹን ዝርዝር የያዙ ኮድ ቡክ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ተሰጥቷል፡፡

- ባለፈዉ ዓመት ለተጠኑት የጎጆ /ዕደ- ጥበብ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናቶችና መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ እና የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናቶች ሰርቬይ ሜቶዶሎጂ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍል የተላለፈ ሲሆን፣ የጥናቶቹ ውጤት አስተማማኝነት በሚመለከት ግምገማ ተካሂዷል፡፡

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ዉጤት የቀሪ ክልሎች ማለትም የቤንሻንጉል፣ የሐረሪ፣ የጋምቤላ፣ የድሬዳዋ አስተዳደር ካዉንስል፣ የኦሮሚያ፣ የአፋር፣ የሱማሌ፣ የአዲስ አበባ መስተዳድርና የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የአገር አቀፍን በተመለከተ ሜቶዶሎጂ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተዉ ክፍል ተሰጥቷል፡፡

- ከ1996 ጥቅምት ወር መጨረሻ ጀምሮ ዝቅ ብሎ በሚበር አዉሮፕላን ለተካሄደዉ የሱማሌ ብሔራዊ ክልል የቤት እንስሳት ቆጠራ ዉጤት አጋዥ የሆነዉን የምድር ላይ ጥናት (Ground truthing survey) ለማከናወን የሚረዳ ሜቶዶሎጂ ከዉጪ ከመጣ አማካሪ ጋር ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲዉል ተደርጓል፡፡

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ማለትም በአፋር ክልል በ23 ወረዳዎች እንዲሁም በሱማሌ ብሔራዊ ክልል በሦስት ወረዳዎች ዉስጥ ለተካሄደዉ የቤት እንስሳት ናሙና ቆጠራ የሚያገለግል አስፈላጊው ሰርቬይ ሜቶዶሎጂ ተሠርቷል፡፡ በሜቶዶሎጂዉ መሠረት ለመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቶ ሥራዉ የተካሄደ ሲሆን፣ በሰርቬይ ሜቶዶሎጂው መሠረት የማባዣ ሥራ ተሠርቷል፡፡

- 1995 በሐምሌ ወር የተካሄደዉን የቤተሰብ ኑሮ ሁኔታ ክትትል ሙከራ ጥናት ዉጤት መሠረት በማድረግ ወደፊት ዋናዉን ጥናት ለማካሄድ የሚረዳ ሜቶዶሎጂ ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የ1996 የሰብል ትንበያ ጥናትና የከተማ ወቅታዊ የሥራ ስምሪት ጥናት ዉጤትን በተመለከተ ማባዣ ተሠርቷል፡፡ በሜቶዶሎጂዉ መሠረት የጥናቶቹ ዉጤት አስተማማኝነት ግምገማ ተካሄዶ የጥናቶቹን ዉጤት የሚገልፅ ሰርቬይ ሜቶዶሎጂ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ከጥናቱ ሪፖርቱ ጋር እንዲታተም ተደርጎ ለሚመለከተዉ ተላልፏል፡፡

- ለኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ የሚያስፈልገው የቤቶችና ቤተሰቦች ምዝገባ እና ካርታን ወቅታዊ የማድረግ መመሪያ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የተሞሉ መጠይቆች የአካባቢ መለያ በኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ወቅት በአግባቡ እንዲከናወን የኮድ ቡክ ዝግጅትና የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራን በተመለከተ ክትትል ተደርጓል፡፡

- ከውጭ በመጡ ባለሙያዎች በተሰጠው የሦስት ሣምንት የ CSpro ስልጠና መሰረት ከግብርና ውጭ ለሚካሄዱት ልዩ ልዩ ሶሽዮ ኢኮኖሚክ ጥናቶች Standard Error (SE) እና Coefficient of Variance(CV) ለማውጣትና የጥናቱን ውጤት አስተማማኝነት ለመገምገም እንዲቻል በCSpro Software የሰፈረውን ፕሮግራም በሚፈለገው መልክ የማሻሻልና አስተማማኝ ውጤት ለማግኘት የሚያስችል ሥራ ተከናውኗል፡፡

- ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ ጥናትና ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የሚያስፈልገው የቤቶችና ቤተሰቦች አመዘጋገብ፣ የቤተሰቦች አመራረጥና ካርታ አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

- ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት እና ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የሚያስፈልገው የቤቶችና ቤተሰቦች አመጋገብ፣ የቤተሰቦች አመራረጥ እና ካርታ አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ከከተማ በተጨማሪ ለተጠቀሱት ጥናቶች በገጠር የሚጠኑትን የ2072 የቆጠራ ቦታዎች ምርጫ በማከናወን ዝርዝራቸው ለ25 ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት በገጠርና በከተማ የተመረጡ የቆጠራ ቦታዎችን የያዘ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቷል።

- ለ1997 ዓ.ም ለሚካሄደው የቋሚ ሰብል፣ የአትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ምርታማነት ጥናት የቤተቦች አመዘጋገብና አመራረጥ መመሪያ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።

- ሰርቬይ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ ለሌሎች መንግስታዊና መንግሥታዊ ላልሆነ ድርጅቶች ቴክኒካዊ ዕገዛ ተደርጓል።

- በመ/ቤቱ ለሚካሄዱ የግብርና ናሙና ጥናትና የወቅታዊ የሥራ ስምሪት ጥናት የ647 ቆጠራ ቦታዎች እንዲሁም ለኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ የ8,682 የከተማ ቆጠራ ቦታዎች ኮፒ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል።

- ለተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የ147 ቆጠራ ቦታዎችና የ136 ወረዳዎች የካርታ ኮፒዎች ሽያጭ ተከናዉኗል።

- የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የተከሰተዉን የአስተዳደር እርከኖች አከላለል ለዉጥ መሠረት በማድረግ ካርታዉን ለማስተካከል የኢንዴክስ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ በጋሙጎፋ ዞን የ13 ወረዳዎች፣ በዳዉሮ ዞን የአምስት ወረዳዎች፣ የባስኬቶና የኮንታ ልዩ ወረዳዎች የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዉ ለንድፍ ተዘጋጅተዋል።

- የግብርና ናሙና ጥናት (መኸር ወቅት) ማባዣ የተዘጋጀ ሲሆን፤ የሰርቬይ ሜቶዶሎጂ ሪፖርት ከጥናቱ ጋር እንዲታተም ለሚመለከተው መምሪያ ተሰጥቷል። የጥናቱን ውጤት አስተማማኝነትም ለማረጋገጥ የውጤት ግምገማ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- ወደፊት ለወረዳ ኔት ፕሮግራም አካል የሆነውን የስታቲስቲክል ሥልጠና በሚመለከት የስታቲስቲክስ ፅንሰ ሃሣቦች እንዲሁም

የመዝገብ አያያዝ ዕንስ ሃሣቦች ዓላማን በተመለከተ የሥልጠና ዶክመንት በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

## 4. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ

### 4.1 የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ዳታ ኢንትሪ

በበጀት ዓመቱ በመ/ቤቱ ለተካሄዱ የተለያዩ አዳዲስና ከ1995 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ከተከናወነላቸው ጥናቶች ውስጥ የ1994 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የ1995 የአከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥናት፣ የ1995 የቤተሰብ ኑሮ ሁኔታ ክትትል ሙከራ ጥናት እንዲሁም የ1996 በጀት ዓመት ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች፣ የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣ የመኸር ወቅት የግብርና ጥናቶች፣ የቤት እንስሳት ናሙና ጥናት፣ የሱማሌና የአፋር የቤት እንስሳት ቆጠራ፣ የተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት (2ኛዙር) ከፊል መረጃዎች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተከናውኗል፡፡

### 4.2 የሠንጠረዥ ዝግጅት

ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት በመ/ቤቱ ለተካሄዱ አዳዲስና ከ1995 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው ለተጠናቀቀላቸው ጥናቶች ማለትም በ1995 ዓ.ም ለተከናወኑ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የጐጆ/የዕደ-ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት፣ የአከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥናትና የቤተሰብ ኑሮ ሁኔታ ክትትል ሙከራ ጥናት፣ እንዲሁም በ1996 ዓ.ም ለተጠኑ የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣ የሱማሌና የአፋር ክልሎች የቤት እንስሳት ቆጠራ፣ ለተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት (1ኛ ዙር) እና ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው የየጥናቱን ውጤት የሚያሳዩ ሠንጠረዦች ተቀነባብረው ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ተልከዋል፡፡ በተመሳሳይ በ1994 ዓ.ም በተከናወነው የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የኮምፒውተር ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ለመምሪያው ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ጥናቶች /ቆጠራ ውጤት አስተማማኝ መለኪያ /CV/ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል፡፡

4.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- የመ/ቤቱን የፐርሰኔል Database Management system (DBMS) ለማቋቋም የሚያስችል መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት፣ ሪፖርቶችን ለማውጣት፣ የዳታ ቤዙን ትክክለኛነትና ወቅታዊነት መከታተልና መቆጣጠር የሚያስችል DBMS የተዘጋጀ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ መረጃዎቹን ወደ ኮምፒውተር ለማስተላለፍ በሚያስችሉ ፎርሞች ላይ የመመዝገቡ ሥራ በመ/ቤቱ የሰራተኛ አስተዳደር ዋና ክፍል አማካኝነት እየተከናወነ ይገኛል።

- የመ/ቤቱን አሰራር በቴክኖሎጂ ለመደገፍ እንዲቻል የLeased Line አገልግሎት መስመር ያገኘ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ መስመሩ ለኢንተርኔት አገልግሎት configure የማድረጉ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል። በመ/ቤቱ የተጀመረው የ Leased Line አገልግሎት ሁሉቱንም ግቢዎች እንዲያገናኝ ለማድረግም በመስመር አልባ መሣሪያዎች ለማገናኘት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

- ከመ/ቤቱ የተለያዩ መንግስታዊ፣ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች መረጃ ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት የተለያዩ ጥናቶች/ ቆጠራዎች ጥሬ መረጃዎችና የሪፖርት ሠንጠረዦች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል።

## 5. የአካባቢ ጽ/ቤቶችና የመስክ ሥራ ክንውንን በተመለከተ

### 5.1 የሰዉ ኃይል ስልጠናን በተመለከተ

- በየዓመቱ በመ/ቤቱ ለሚካሄዱት የተለያዩ ጥናቶች ለአሰልጣኞችና ለመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ይካሄዳል። በመሆኑም በ1996 ዓ.ም ለግብርና ናሙና ጥናቶች፣ የግብርና ምርቶች የአምራች ዋጋ ጥናትና ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት የአሰልጣኞች ስልጠና ከዋናዉ መ/ቤትና ከቅ/ጽ/ቤቶች ለተዉጣጡ 45 ፕሮፌሽናሎችና 51 መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች ከሐምሌ 28 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 6 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ስልጠና በዋናዉ መ/ቤት ተሰጥቷል። በተመሣሣይ በእነዚህ ጥናቶች ላይ ለሚሣተፉ 2,313 መረጃ ሰብሳቢዎችና 447 የመስክ ተቆጣጣሪዎች በቅ/ጽ/ቤቶች ከነሐሴ 9 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 26 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷቸዉ፤ በዋናዉ

መ/ቤት የተዘጋጀዉን የተሣታፊዎች የግንዛቤ መመዘኛ የጽሑፍ ፈተና ከወሰዱ በኋላ ብቃት ያላቸዉና ፈተናዉን ያለፉ የመስክ ሠራተኞች ወደ ሥራዉ እንዲገቡ ተደርጓል::

- በጥቅምት ወር 1996 ዓ.ም ጀምሮ ለተካሄደዉ የወቅታዊ የሥራ ስምሪት ጥናት የአሰልጣኞች ሥልጠና ከመስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ በዋናዉ መ/ቤት ከ22 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተዉጣጡ 35 ባለሙያዎች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በተመሣሣይ በ13 አማካይ ቅ/ጽ/ቤቶች ላይ ለ247 መረጃ ሰብሳቢዎችና ለ66 ተቆጣጣሪዎች ከጥቅምት 5 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 11 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቶ የጥናቱ መረጃ መሰብሰብ ተግባር ከጥቅምት 13 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ኅዳር 10 ቀን 1996 ዓ.ም ደረስ ተካሂዷል::

- የ1994 ግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራ ለሆነዉና በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለተካሄደዉ የቤት እንስሳት ቆጠራ በአፋር ብሔራዊ ክልል ለሚሣተፉ ሠራተኞች የአሠልጣኞች ስልጠና በዋናዉ መ/ቤት ለ23 የወረዳ አስተባባሪዎች፣ ለሁለት የዞን አስተባባሪዎችና ለ12 አሠልጣኞች የአንድ ቀን ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ በአራት ቅ/ጽ/ቤቶች (አሣኢታ፣ ደብረብርሃን፣ ደሴና መቀሌ) ለ303 መረጃ ሰብሳቢዎችና ለ54 ተቆጣጣሪዎች ከታህሣስ 22 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ስልጠና ተሰጥቷል::

- ከየካቲት 22 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዚያ 14 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ለሚካሄድለትና ለመጀመሪያ ጊዜ በመካሄድ ላይ ላለው የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ለሚሳተፉ 49 ባለሙያዎች ያሰልጣኞች ስልጠና ከየካቲት 8 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ የካቲት 11 ቀን 1996 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት የተሰጠ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ በ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በስራው ላይ ለሚሳተፉ 3825 የመስክ ሰራተኞች ከየካቲት 15 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 20 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ስልጠና ተሰጥቷል::

- ከሰኔ 15 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 27 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ለተካሄደለት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናትና ከሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ለሚካሄድለት የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት በዋናው መ/ቤት

ከሚያዝያ 25 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ግንቦት 12 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ከ150 በላይ ለሆኑ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተመሳሳይ በነዚህ ጥናቶች ላይ ለሚሳተፉ ከ4800 በላይ የመስክ ሰራተኞች ከግንቦት 17 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 11 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ሥልጠናና የመስክ ልዩ ልምምድ ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

## 5.2 የመስክ ሥራን በተመለከተ

- በሱማሌና በአፋር ብሔራዊ ክልሎች ለተደረገዉ የቤት እንስሳት ቆጠራ ከአሜሪካ የልማት ዕርዳታ ድርጅትና በመንግሥት በተገኘ ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ በሱማሌ ክልል ዝቅ ብሎ በሚበር አዉሮፕላን የቤት እንስሳት ቆጠራ ሥራዉ ከጥቅምት 28 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ኅዳር 12 ቀን 1996 ዓ.ም በሽንሌ፣ በፊቅ፣ በደገሀቡር፣ በጎዴ፣ በዋርዴርና በአፍዴር ዞኖች ላይ ተካኄዷል፡፡ በተመሣሣይ ይህንኑ የሥራ ሁኔታ ለመደገፍ በመደበኛዉ የቆጠራ ሥራ በክልሉ በተመረጡ አምስት ወረዳዎች ላይ 25 መረጃ ሰብሳቢዎችን፣ አምስት ተቆጣጣሪዎችን እንዲሁም አምስት አስተባባሪዎችን በማሰማራት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም በቆጠራዉ ባልተሸፈኑ የክልሉ ሦስት ወረዳዎች (በሀርሽን፣ በባቢሌና በጉርሱም) ላይ ከታህሣሥ 7 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 20 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ 60 መረጃ ሰብሳቢዎችና 11 ተቆጣጣሪዎችን በማሰማራት በወረዳዎቹ የቤት እንስሳትን በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ ተግባር ተካሂዷል፡፡

- በአፋር ብሔራዊ ክልል ለሚካሄደዉ የቤት እንስሳት ቆጠራ ተግባር የመረጃ መሰብሰብ ሥራዉ ከታህሣሥ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በወጣለት መርሃ-ግብር መሠረት በክልሉ ሁሉም ወረዳዎች የቆጠራ ሥራዉ ተካሂዷል፡፡

## 5.3 ለቅ/ጽ/ቤቶች የተሰጠ ድጋፍን በተመለከተ

- በመ/ቤቱ ስር ለተቋቋሙት 25 ቅ/ጽ/ቤቶች አስፈላጊ የሆነዉን የካፒታል በጀት ጥያቄ በየወሩ እያዘጋጀ በማቅረብ እንዲላክላቸዉ ያደረገ ሲሆን፤ እስከ መጋቢት ወር 1996 ዓ.ም ድረስ 19,563,431 ብር ተልኮላቸዋል፡፡

- ከዋናዉ መ/ቤት የሚመለከታቸዉ መምሪያዎች ጋር በመሆን በሰዉ ኃይል ቅጥር፣ ለመስክ ሥራ በሚያገለግሉ መጠይቆች፣ መመሪያዎችና የሎጂስቲክስ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ ሲሆን፤ በመስክ ሥራ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች በወቅቱ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

- በ1996 በጀት ዓመት መ/ቤቱ በሚያካሂዳቸዉ የተለያዩ ጥናቶች ላይ በአሠልጣኝነት የተሣተፉ የዋናዉ መ/ቤት ባለሙያዎችንና ጥናቶቹ በቀጥታ የሚመለከታቸዉ የመምሪያ ባለሙያዎች የመስክ ቁጥጥርና ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ የ1996 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናትና የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ ከመስከረም 11 ቀን 1996 እስከ መስከረም 22 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የዋናዉ መ/ቤት ባለሙያዎች በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የመስክ ሥራ ቁጥጥርና ግምገማ ሥራ አካሂደዋል። በተመሣሣይ ሁኔታ ለከተማ ወቅታዊ የሥራ ስምሪት ጥናት በሁለት ዙር ለ13 ቀናት የመስክ ጉብኝት ከዋናዉ መ/ቤት በአሠልጣኝነት በተሣተፉ ባለሙያዎች ተካሄዶ የሙያ ድጋፍ ለጽ/ቤቶቹ የመስክ ሠራተኞች ተሰጥቷል። እንዲሁም ከየካቲት 22 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ላለው የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ የዋናው መ/ቤት የማኔጅመንት አባላትና ባለሙያዎች ከመጋቢት 8 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ አስር ቀናት የመስክ ቁጥጥርና የሙያ ድጋፍ አድርገው ተመልሰዋል።

- ከሰኔ 5 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ 13 ቀናት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ለተካሄደለት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት እና ከሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር እየተካሄደለት ላለው ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ከዋናው መ/ቤት በአሰልጣኝነት ተመድበው የነበሩ ባለሙያዎችና ቴክኒሽያኖች በተመደቡበት ቅ/ጽ/ቤቶች በመቆየት ለመስክ ሥራው ሙያዊ ድጋፍ አድርገዋል።

## 6. የ1996 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

በ1996 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ከ1995 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎችንና በ1996 ዓ.ም ደግሞ አዳዲስ ጥናቶችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና በበጀት ዓመቱ እነዚህን ጥናቶች በተመለከተ ያከናወናቸዉን ሥራዎች በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል። የእነዚህን የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚመለከት የፊዚካል አፈፃፀም ሠንጠረዥ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1 በ1996 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1995 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የ1996 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | የ1996 የግብርና ናሙና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 100 |
| 1.2 | የሰብል ሁኔታ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ጥናት | አዲስ | - | 100.0 | 100.0 | 100 |
| 1.3 | የቋሚ ሰብሎች አትክልትና ሥራሥር ተክሎች አጨዳ ሙከራ ጥናት* | አዲስ | - | 15.0 | 15.0 | 100 |
| 1.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት | | | | | |
| | • የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 100 |
| | • የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 100 |
| | • የመሬት አጠቃቀም | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 88.25 | 95 |
| | • የቤት እንስሳት ናሙና ጥናት | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 100 |
| 1.5 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | አዲስ | 6.75 | 58.25 | 58.25 | 100 |
| 1.6 | የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት | አዲስ | 6.75 | 53.25 | 43.25 | 81 |
| 1.7 | የግብርና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች | | | | | |
| | • የሱማሌ ክልል የቤት እንስሳት ቆጠራ | ነባር | - | 100.0 | 100.0 | 100 |
| | • የአፋር ክልል የቤት እንስሳት ቆጠራ | ነባር | - | 100.0 | 100.0 | 100 |
| 2 | የኢኮኖሚ ተቋማት አጠቃላይ ቆጠራ | | - | 80.0 | 80.0 | 100 |
| 3 | የ1995 የትላልቅና መካከ. ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | አዲስ | - | 75.0 | 70.0 | 93 |
| 4 | ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት | አዲስ | 6.00 | 84.0 | 77.0 | 92 |
| 5 | የግብርና ዉጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት | አዲስ | 9.00 | 91.0 | 91.0 | 100 |
| 6 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 15.00 | 85.0 | 85.0 | 100 |
| 7 | ከ1995 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎች | | | | | |
| 7.1 | የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ጥናት | ነባር | 85** | - | 15.0 | - |
| 7.2 | የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት | ነባር | 85** | - | 15.0 | - |
| 7.3 | መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት | ነባር | 85** | - | 15.0 | - |
| 7.4 | የአከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥናት | ነባር | 85** | - | 10.0 | - |
| 7.5 | የ1994 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት | ነባር | 80** | - | 20.0 | - |
| 8 | የኢንዴክስ ዝግጅት | | | | | |
| 8.1 | የአዲስ አበባ | አዲስ | - | 100.0 | 100.0 | 100 |
| 8.2 | የአገር አቀፍና ክልሎች | አዲስ | - | 100.0 | 90.0 | 90 |

* ወደ 1997 ዓ.ም የተሸጋገረ ነዉ::
** ከ1995 ዓ.ም የተሸጋገሩ ጥናቶች::

## 7. የ1995 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎችን የሚያካትት ዓመታዊ መጽሔት ያዘጋጃል። ለዚህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸዉ የፌደራልና የክልል መ/ቤቶች እንዲሁም ድርጅቶች በአብዛኛዉ ተሰብስቦና የሠንጠረዥ ሥራዉ በሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭ ሲሆን፤ የ1995 ዓ.ም ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔትም በተመሣሣይ ሁኔታ የመረጃ መሰብሰቡና ማጠናቀሩ ሥራ ተከናዉኖ በመታተም ላይ ይገኛል። ይህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያካትት ተደርጎ ተዘጋጅቷል። እነዚህም

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የዉጭ ንግድ መረጃዎች፣
- ዓመታዊ የሃገር ሃብት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የመድህን /ኢንሹራንስ/ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የስፖርትና ሲኒማ መረጃዎች፣... ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።

## 8. <u>የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት</u>

- በተሻሻለው የውጤት ተኮር የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም መመሪያ ይዘትን በሚመለከት ለዋናዉ መ/ቤት ከሐምሌ 22-28 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚያስችል ሥልጠና ተሰጥቷል። በዋናዉ መ/ቤትም ሆነ በቅ/ጽ/ቤቶች ሥልጠናዎቹ ሲካሄዱ የመ/ቤቱ የ1996

ዓ.ም ዉጤት ተኮር የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም መለኪያዎችና መርሐ-ግብር ተዘጋጅቶ ለግንዛቤ እንዲሆን በምሳሌነት ቀርቧል።

- የሥራ ውጤት ማሻሻያን በሚመለከት የ1996 በጀት ዓመት የተዘጋጀው የሥራ ዕቅድ መነሻ በማድረግ በተዋረድ ለሥራ ዘርፎች፣ ለቡድኖች፣ ለሥራ ክፍሎችና ለዕቅድ ፈፃሚ ሠራተኞች የቁልፍ፣ የአበይትና ንዑሣን ተግባራት የዕቅድ አፈፃፀም መለኪያዎች መርሃ ግብር ለተወሰኑ የሥራ ክፍሎች ቡድኖችና የጥቂት ዕቅድ ፈፃሚ ሠራተኞች ተዘጋጅቷል።

- በመ/ቤቱ ዉስጥ ከሚገኙ የመስመር መምሪያዎች መካከል የሁለት መምሪያዎችን የሰዉ ኃይል፣ የቢሮ አመችነትና ከሌሎች ተጓዳኝ የሥራ ክፍሎች ጋር ያላቸዉን የሥራ ግንኙነት በሚመለከት በጠይቅ ተዘጋጅቶና አስተያየት ተሰብስቦና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

- የመ/ቤቱ የማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት አገልግሎት ደረጃ ለማሻሻልና የመ/ቤቱ ሾፌሮች ከሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ጋር የተጣጣመ የስራ መደብ እንዲኖርና እንዲፈቀድ እንዲሁም የነገረፈጅ መፕ-9 የሥራ መደብን ወደ መፕ-8 ዝቅ ለማድረግ /ተቀጣሪ ሠራተኛ ማጣት ምክንያት/ ጥያቄ ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ የአገልግሎቱ ሁለት፣ የሾፌሮች አስር የሥራ መደብ የተፈቀደ ሲሆን፤ የነገረፈጅ የሥራ መደብም በጥያቄው መሠረት ተስተካክሏል።

- መ/ቤቱ የዳታ ኢንትሪና የኤዲቲንግ ሥራዎች በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል እንዲካሄዱ ለማድረግ የስታቲስቲሺያን መደቦች በ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለእያንዳንዳቸው 25 ፕሣ-2 እና ፕሣ-3, አስር ፕሣ-4 እንዲሁም 15 ፕሣ-5 የሥራ መደብ እንዲፈቀድ ጥያቄው ለሲቪል ስርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ፤ የሲቪል ሰርቪስ ባለሙያዎች በዋናው መ/ቤት ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በጥያቄው ላይ ውይይት ያካሄዱ ሲሆን፤ ወደ አምስት ቅ/ጽ/ቤቶች በመሄድ የሥራ ሁኔታዎችን እንዲመለከቱ ተደርጓል።

- የመ/ቤቱን ተሽከርካሪዎች አጠቃቀምና የጥገና ሥራ ከማከፈለው ክፍያ ጋር ያለውን መጣጣምና ተቃርኖ ለማወቅና የመፍትሄ ርምጃ

ለመዉሰድ አመች ሁኔታን ለመፍጠር መረጃዎች ተሰብስበውና ተጠናቅረዉ የመ/ቤቱ የሚመለከታቸዉን የሥራ ክፍሎች በተገኙበት ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መረጃ መሰረት መኪናዎቹ በምንም ዓይነት መንገድ ቢጠገኑ ለመ/ቤቱ አዋጭ ሊሆን ይችላል የሚለውን ጭብጥ ለማግኘት ጥናት እንዲካሄድ በተደረሰው ስምምነት መሰረት ጥናቱ ተጀምሯል፡፡

- በቅ/ጽ/ቤቶች በብልሽት ምክንያት ለአገልግሎት ብቁ ያልሆኑትን የመስክ ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ወጪ ለጥገና በሚመጡበት ጊዜ ጋራዥ እስከሚገቡ ወይም ኢንሹራንስ እስከሚረከባቸው ድረስ ያለው የአሰራር ሂደት ተገምግሞ የአሰራሩ ማሻሻያ ላይ የቀረበ ሲሆን ቀሪው ሥራ በቀረበው ማሻሻያ ላይ ተነጋግሮ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

- የመ/ቤቱ የእቃ ግዥ አፈጻጸም ለመገምገም የሚያስችል የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ተሰብስበውና ሪፖርቱ ተጠናቅሮ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች በተገኙበት ውይይት ተደርጎ በምን መልክ ግዥው ቢፈጸም እንደሚሻል ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የግዢው አፈጻጸም ወርሃዊ ሪፖርትም ለመ/ቤቱ የስነ-ምግባር መኮንን እንዲደርስ እየተደረገ ነው፡፡

- የመ/ቤቱን ሠራተኞች የመፈፀም አቅም በሥልጠና ለማጐልበት በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ተቋም ክፍያ ተፈፅሞ አንድ የሥራ ክፍል ሃላፊና 6 የዕቅድ ፈጻሚ ባለሙያዎች ስልጠናውን የተከታተሉ ሲሆን 9 ባለሙያዎች ተቋሙ የዕቅድ ለውጥ በማድረግ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት እንዲሰለጥኑ አስተላልፏል፡፡

- የባለጉዳዮችን አገልግሎት አሰጣጥና ቅሬታ ማስተናገጃን በሚመለከት የመ/ቤቱን ድርጅታዊ ብቃት ለመገምገም የሚያስችል ከሰራተኛው አስተያየት ተሰብስቦ መረጃው በኮምፒውተር ተቀነባብሮ በተቋቋመው ግብረ-ሃይል የትንተናው ሥራ ተጠናቆ ረቂቅ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል፡፡

- የዉጭ ተገልጋዮች በመ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን በተገቢው ጊዜ ለማግኘት በቅድሚያ ማሟላት የሚገባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያሳዉቅ ጽሁፍ በመ/ቤቱ የዜና መጽሔት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል የዉጭ ተገልጋዮች መ/ቤቱ በሚሠጣቸዉ አገልግሎቶች

አሠጣጥ ላይ ያላቸዉን አስተያየትና ቅሬታ ለማሰባሰብ በታቀደዉ መሠረት መጠይቆች ተዘጋጅተው ለዋና ዋና መረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭተው መረጃ ተሰብስቧል።

- በሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የስነ - ምግባር መኮንን የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ባዘጋጀዉ የሁለተኛ ዙር ስልጠና ላይ ከሐምሌ 20-23/95 ዓ.ም ድረስ ተሳትፈዋል። የመ/ቤቱ የስነ ምግባር ደንብ ዝግጅት ተጠናቆ የፌደራል ስነ-ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል።

## 9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

- በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 215 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቶች፣ 9 የቤተሰብ በጀት ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ 23 የሰዉ ኃይል ጥናት፣ 35 የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት፣ 5 የስነ ሕዝብና ጤና ጥናት፣ 814 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ጥናት ውጤት፣ 3,009 የዋጋ ጥናት፣ 262 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ 238 የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ 237 የጎጆ /እደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ 235 መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት /Urban Informal Sector/፣238 የትራንስፖርትና መገናኛ ጥናት፣ 238 የአከፋፋይ ንግድ ጥናት፣ 13,641 የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት፣ 20 የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ደህንነት ጥናት፣ 225 በከተሞች የሥራ ስምሪት ጥናት፣ 241 የውጭ ንግድ ጥናት፣ 19 የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት፣ በጠቅላላው 19,704 ሪፖርቶች ለመንግስት ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከላት በነጻ ተሰራጭቷል።

- በሌላ በኩል 360 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቶች፣ 74 የቤተሰብ በጀት ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ 52 የሰዉ ኃይል ጥናት፣ 27 የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናት፣ 26 የስነ-ህዝብና ጤና ጥናት፣ 590 የህዝብና ቤት ቆጠራ፣724 የዋጋ ጥናት፣ 93 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ 76 የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ 59 የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ 45 መደበኛ የልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት፣ 80 የውጭ ንግድ ጥናት፣ 27 የትራንስፖርትና መገናኛ ጥናት፣ 29 የአከፋፋይ ንግድ ጥናት፣ 1,012

የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት፣ 104 የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ 10 የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት፣ 7 በከተሞች የሥራ ስምሪት ጥናት፣ በጠቅላላው 3,395 ሪፖርቶች በብር 98,138 ሽያጭ ተፈጽሟል።

- የመ/ቤቱ ቤተመፃሕፍት ለመ/ቤቱ ሠራተኞችና ለዉጭ ተገልጋዮች የንባብና መረጃ የመስጠት አገልግሎት ተግባር እያከናወነ ነው፤ በዚህም መሰረት የአገልግሎቱን አድማስ ለማስፋትና አቅሙን ለማጎልበት በበጀት ዓመቱ 33 የተለያዩ አዳዲስ መፃሕፍትን በግዥ፣ 153 መጽሔቶችን በኮንትራት ግዥ 182 መጻህፍትንና መጽሔቶችን በግዥ እንዲሁም 182 መጻህፍትንና መጽሔቶችን በዕርዳታና በስጦታ በማሰባሰብና 449 የመ/ቤቱን የጥናት ሪፖርቶች በመረከብ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለማርካት ጥረት ተደርጓል።

- በ1996 በጀት ዓመት በመ/ቤቱ የተለያዩ የመስመር መምሪያዎች ለተካሄዱ የግብርና፣ የዋጋ ጥናት፣ የኢንዱስትሪ፣ የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናትንና መሰል ጥናቶችን በሚመለከት ስለመረጃዎቹ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ የአሰራር ሂደት ለህብረተሰቡ ግንዛቤን ለማስጨበጥ የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል። በተመሳሳይ በአፋርና በሱማሌ ብሔራዊ ክልሎ የተካሄዱትን የቤት እንስሳት ቆጠራና በመላው አገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደውን የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ የሚመለከት በአማርኛ፣ በአፋርኛና በሱማሌኛ ቋንቋ ብሮሹሮች ተዘጋጅተው ተሰራጭቷል።

- የ1996 አዲስ ዓመት ምክንያት በማድረግ 4,000 የግድግዳና 5,000 የኪስ የቀን መቁጠሪያ ተዘጋጅተዉ ከመ/ቤቱ ጋር ግንኙነት ላላቸዉ አካላትና ለመ/ቤቱ ሠራተኞች በማሠራጨት የመ/ቤቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል።

- በበጀት ዘመኑ ለመጀመሪያ ጊዜ የመ/ቤቱን ልሣን የሆነዉ "ልሣነ ማ.ስ.ባ." መጽሔት ቁጥር አንድና ቁጥር ሁለት እያንዳንዳቸው በ2,000 ኮፒ ታትሞ ተሠራጭቷል። በተመሳሳይ «ዜና ማስባ» ቅጽ 1 ቁጥር 1 እና 2 ተዘጋጅተው እያንዳንዳቸው በ2,000 ኮፒ ታትመው ተሠራጭተዋል።

- በመ/ቤቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን፣ ስልጠናዎችን፣ ስብሰባዎችን፣ የመስክ ሥራ ጉብኝቶችን ....ወዘተ በፎቶግራፍና በቪዲዮ ተቀርጸው እንዲቀመጡ ተደርጓል። እንዲሁም የመ/ቤቱን ታሪካዊ አመሰራረት የሥራ ሂደት በተመለከተ ለመረጃነት የሚያገለግል ሰነድ ለማዘጋጀት ቅድመ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው።

## 10. <u>የኦዲት አገልግሎት</u>

- የ1996 ዕቅድ ዘመን የመ/ቤቱ የ1995 በጀት ዓመት ዝርዝር የሂሣብ ምርመራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል። የ1995 ዓ.ም የንብረት ምርመራና በከፊል የንብረት ቆጠራ ተደርጐ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች አንድ በአንድ ተቆጥረው ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን፣ የ1996 ዓ.ም የሂሳብ ምርመራ በመካሄድ ላይ ነው።

- በመ/ቤቱ የሚካሄዱትን የጥናት ሪፖርቶች ሽያጭና ስርጭት በሚመለከት በንብረት ክፍሉ ወጪ በተደረገው መሰረት ቆጠራና ምርምር ተደርጐ የዘጠኝ ዓመት አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በተመሳሳይ የ1996 በጀት የመጽሔት ቆጠራ ተካሂዶ የምርመራ ሥራው በመካሄድ ላይ ሲሆን የ1996 ንብረት ቆጠራና የምርመራ ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- የመ/ቤቱ አንድ ዘርፍ የነበረዉ የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ይጠቀምበት የነበረዉን ንብረት በመመርመርና በማጣራት የርክክብ ተፈጽሞ ሪፖርት ቀርቧል።

- የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ከቦታቸዉ በመነሳታቸዉ ምክንያት ያንቀሣቅሱት የነበረዉን ጥሬ ገንዘብና ንብረት ምርመራ ተደርጐ ለተተኪዉ ኃላፊ የማረካከብ ሥራ ተካሂዷል፤ በተመሳሳይ የሆሳዕና ቅ/ጽ/ቤት ሒሳብ ሠራተኛ ወደ ሌላ የሥራ መደብ በመዛወራቸው ምክንያት ያንቀሣቅሱት የነበረዉን የጽ/ቤቱን የሒሳብ ሰነድ ኦዲት በማድረግ ለተተኪው ሠራተኛ ርክክብ ተፈጽሟል።

- በዋናው መ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ፣ በፋይናንስ ክፍል የሂሳብ ማስረጃዎችንና መዛግብትን የያዙ ሰራተኞችና በዚሁ ክፍል አካውንታንት የነበሩ ሰራተኞች ይንቀሳቀሳሉ የነበሩ የሂሳብ

ማስረጃዎች ጉርድ ቸኮችና ሥራ ላይ ያልዋሉ ቸኮችና ሰነዶች የምርመራ ሥራ ተካሂዶ ለተተኪዎቹ ርክክቡ ተፈጽሟል::

## 11. ሕግ አገልግሎት

- የመ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩበት ወቅት በተለያየ ጊዜያትና በተለያዩ ምክንያት ያጎደሉትን የመንግሥት ገንዘብና መ/ቤቱ ለትምህርት ወደ ዉጪ የላካቸው ባለሙያዎች ትምህርታቸዉን አጠናቀዉ ሲመለሱ በገቡት ግዴታ መሠረት መ/ቤቱን ባለማገልገላቸዉ ሳይሠሩ የተከፈላቸዉን ደመወዝ ተመላሽ እንዲያደርጉ በተጠየቁት መሰረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 18,552.24 ገቢ ተደርጓል::

- የተለያዩ ግለሰቦች መ/ቤቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍላቸው በተለያዩ ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍ/ቤቶች በብር 206,542.61 ክስ መስርተው ክትትል እየተደረገ ይገኛል:: በተመሳሳይ ብር 252,000 የጉዳት ካሳ የጠየቁ የሁለት ግለሰቦች ክስ በይግባኝ ተሸሮና ውሳኔ ከተሰጠበት ከኋላ እንደገና በብር 179,520 ክስ በፍርድ ቤት እየታየ ይገኛል::

- በሌላ በኩል መ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩበት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች የመንግስት ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው ባዋሉ ግለሰቦች ላይ የብር 133,896.30 ክስ ተመስርቶባቸው እስካሁን በተደረገው ክትትል ብር 64,771.35 እንዲከፍሉ በፍርድ ቤት ተወስኖ ብር 2,880 ገቢ ሲደረግ የቀሪዉን ብር በአፈጻጸም ገቢ እንዲሆን ክትትል እየተደረገ ነው:: በተጨማሪም በተለያየ ምክንያት ሁለት ግለሰቦች መ/ቤቱ ሊከፍለን ይገባል በማለት በብር 762 እና በብር 13,400 ያቀረቡት ክስ የብር 762 ፍ/ቤቱ መ/ቤቱን በነጻ ያሰናበረው ሲሆን የብር 13,400 ክስ ገና በቀጠሮ ላይ የሚገኝ ነው::

## 12. ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1996 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂደዉ አንድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከመንግሥት የተፈቀደዉን ካፒታል በጀት ከሚመለከታቸዉ መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በፊዚካል መርሃ-ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል አስተላልፏል::

- የመ/ቤቱን ወርሃዊ የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት እንዲሁም የመ/ቤቱን የሦስት፣ የስድስትና የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተዉ ክፍል አስተላልፏል።

- የመ/ቤቱ የ1997 - 2001 (የአምስት ዓመት) የስትራቴጂክ ዕቅድና ሥራ አመራር ዶክመንት ከሚመለከታቸዉ የመምሪያና አገልግሎት ኃላፊዎች ጋር በመሆን እየተዘጋጀ ይገኛል።

- በ1996 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለማካሄድ ላቀደዉ የአርብቶ አደሩ አካባቢ የቤት እንስሳት ቆጠራ ማስፈፀሚያ በጀት ከሚመለከታቸዉ መምሪያዎች ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከአስፈላጊ ማብራሪያ ጋር ተዘጋጅቶና ቀርቦ በጀቱ ተፈቅዶ ሥራ ላይ ዉሏል።

- ቅ/ጽ/ቤቶች ለፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚላክላቸዉን የካፒታል በጀት ለመከታተል የሚያስችል የወርሃዊ የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ከሚመለከታቸዉ የሥራ ክፍሎች ጋር በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲዉል አድርጓል።

- የባለስልጣኑን መ/ቤት የሦስት ዓመት (1997- 1999) የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ዕቅድ እንዲሁም የ1997 በጀት ዓመት የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድና የካፒታል በጀት ፍላጎት ከሚመለከታቸው መስመራዊ መምሪያዎችና የሥራ ክፍሎች ጋር በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርቧል።

## 13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት

### 13.1 የሰዉ ኃይል ሁኔታ

በ1996 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,465 ቋሚና 520 የኮንትራት በጠቅላላዉ 1,985 ሠራተኞች ነበሩ። ከቋሚ የመ/ቤቱ ሰራተኞች መካከል እስከ ሰኔ 30 /1996 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ 58 ሰራተኞች በራሳቸው ፍቃድና ስድስት ሰራተኞች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች መ/ቤቱን ሲለቁ 17 ሰራተኞች ደግሞ በሞት ተለይተዋል። እንዲሁም በበጀት

ዓመቱ የ149 አዲስ ሰራተኞች ቅጥር ተፈፅሟል:: በመሆኑም አሁን ያለው የቋሚ ሰራተኞች ቁጥር 1,533 ነው:: እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከነበሩት 520 የኮንትራት ሰራተኞች ውስጥ እስከ ሰኔ 30/1996 መጨረሻ ድረስ ሶስት ተላላኪና የፅዳት ሰራተኞች፣ ስምንት ጥበቃ፣ 32 ሹፌሮች፣ ሶስት የፐርሰኔል ሰራተኞች፣ ዘጠኝ የሂሳብ ሰራተኞች፣አንድ ገንዘብ ያዥ 4,523 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 35 የዳታኢንትሪ ኦፐሬተሮችና 35 የኤዲቲንግና ኮዲንግ፣ ስምንት ጀማሪ ስታቲስቲሽያኖችና ሶስት የመካኒክ ሰራተኞች በጠቅላላው 4,660 አዲስ ቅጥር ሲፈጸም፣ 2,612 ኮንትራት ሰራተኞች ከመ/ቤቱ ተሰናብተዋል:: በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ሃይል በሚከተሰለው ሠንጠረዥ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 2 የሰዉ ኃይል ሁኔታ

| ተ.ቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,465 | 520 | 1,985 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 149 | 4,660 | 4,809 |
| 3 | ሥራ የለቀቁ | (63) | (2612) | (2673) |
| 4 | በጡረታ የተገለሉ | - | - | - |
| 5 | በሞት የተለዩ | (17) | - | (17) |
| | ድምር | 1,533 | 2,568 | 4,101 |

## 13.2 የበጀት አጠቃቀም

ለ1996 በጀት ዓመት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግስት የተፈቀደለት የመደበኛና የካፒታል በጀት በጠቅላላው ብር 50,073,600 ነው:: ከዚህ ውስጥ ብር 14,912,100 ለመደበኛ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ የሚውል ሲሆን ብር 35,161,500 ለብሔራው የተቀናጀ ሰርቬይ የካፒታልና የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ነው::

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

በ1996 የዕቅድ ዘመን ለመደበኛ ሥራ ማስፈጸሚ ከተፈቀደው ብር 14,912,100 ውስጥ ብር 13,324,200 ለደመወዝ፣ ብር 1,587,900 ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የሚውል ነው::

በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ ብር 13,423,505.88 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 13,206,637.58 ሥራ ላይ ውሏል ሥራ ላይ ከዋለው ገንዘብ ውስጥ 11,835,605.88 (89.6%) ለደመወዝ የተከፈለ ሲሆን ብር 1,371,031.70 (10.38%) ለሥራ ማስኬጃ የዋለ ነው። በጠቅላላው ለዓመቱ ከተመደበው በጀት ሥራ ላይ የዋለው 88.56% ያህል ነው።

ሠንጠረዥ 3 የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

| የወጪ ርዕስ | ለዓመቱ የተመደበ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደዉ ዉስጥ ተጠይቆ የመጣ | ተጠይቆ ገቢ ከሆነዉ ዉስጥ ሥራ ላይ የዋለ | የአፈፃፀም በመቶኛ ከዓመቱ |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| ደመወዝ | 13,324,200 | 11,835,605.88 | 11,835,605.88 | 88.82 |
| ሥራ ማስኬጃ | 1,578,900 | 1,587,900.00 | 1,371,031.70 | 86.34 |
| ድምር | 14,912,100 | 13,423,505.88 | 13,206,637.58 | 88.56 |

ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም

በ1996 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚያካሂደዉ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮጀክት ብር 35,161,500 የካፒታል በጀት ተፈቅዶለታል። በዚሁም መሠረት ከሐምሌ 1/1995 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ብር 35,161,500 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 33,583,305.24 ሥራ ላይ ዉሏል ሥራ ላይ የዋለዉ ገንዘብ ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደዉ አጠቃላይ በጀት ጋር ሲነፃፀር 95.5% እንደሆነ ያመለክታል።

ሐ. የውጪ ዕርዳታ በጀት አጠቃቀም

በ1996 በጀት ዓመት በባለሥልጣን መ/ቤቱ ለተካሄዱት ሁለት ጥናቶች ማለትም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነትና የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ማስፈፀሚያ ብር 10.5 ሚሊዮን ወጪ የተደረገ ሲሆን፤ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት በ1997 በጀት ዓመት ታህሳስ ወር ላይ ሁለተኛ ዙር የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የሚካሄድ በመሆኑ ወጪው ከዚህ እንደሚጨምር ይጠበቃል።

## የ1996 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 4

| የሂሣብ መደብ | ለ1996 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተፈቀደና የተስተካከለ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደዉ ዉስጥ በዕቅድ ዘመኑ ተጠይቆ በእጅ የገባ | ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ከገባዉ ሥራ ላይ የዋለ | ከዓመቱ አጠቃቀም በመቶኛ 04/02 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 6113 | 10,154,700 | 10,154,700 | 10,179,908 | 100.2 |
| 6114 | 1,864,800 | 1,864,800 | 1,615,129 | 86.6 |
| 6121 | 28,500 | 28,500 | - | - |
| 6123 | 1,040,953 | 1,040,953 | 936,650 | 90.0 |
| 6212 | 222,500 | 222,500 | 203,362 | 91.0 |
| 6213 | 340,000 | 340,000 | 228,398 | 67.0 |
| 6217 | 1,952,500 | 1,952,500 | 1,842,933 | 94.0 |
| 6231 | 11,450,100 | 11,450,100 | 11,290,240 | 98.6 |
| 6232 | 835,600 | 835,600 | 585,441 | 70.0 |
| 6241 | 4,466,747 | 4,466,747 | 4,466,624 | 99.9 |
| 6243 | 180,000 | 180,000 | 9,645 | 9.4 |
| 6251 | 65,600 | 65,600 | 65,562 | 99.9 |
| 6252 | 377,500 | 377,500 | 310,601 | 82.2 |
| 6253 | 132,500 | 132,500 | 26,000 | 19.6 |
| 6254 | 1,347,700 | 1,347,700 | 1,347,250 | 99.9 |
| 6256 | 100,000 | 100,000 | 60,218 | 60.2 |
| 6257 | 75,000 | 75,000 | 42,832 | 57.1 |
| 6258 | 360,000 | 360,000 | 239,135 | 62.4 |
| 6259 | 78,000 | 78,000 | 84,331 | 108 |
| 6271 | 84,300 | 84,300 | 49,046 | 58.2 |
| 6313 | 4,500 | 4,500 | - | - |
| ድምር | **35,161,500** | **35,161,500** | **33,583,305** | **95.5** |

## 13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ጉዳዮች

### 13.3.1 የጠቅላላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- ለ1996 በጀት ዓመት በዋናዉ መ/ቤትና በየቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸዉን ሠራተኞች በማጣራትና መረጃዎችን በማሰባሰብ በጋዜጣ በግልጽ ጨረታ በማውጣት አሸናፊዉን በጨረታ ኮሚቴ በመለየት ግዥዉ ተፈጽሞ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸዉ የሕትመት መሳሪያዎችን ለአንድ ዓመት በኮንትራት እንዲጠገኑ ለማድረግ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊዉ የመለየት ሥራ እየተካሄደ ነዉ።

- ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ወደ ህዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚሽን የተዛወሩ ሠራተኞች ይገለገሉባቸዉ የነበሩትን ቋሚ ዕቃዎች ርክክብ ተፈጽሟል።

- በ1995/96 ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ሪፖርቶችን ከ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በማሰባሰብ በአንድ ላይ ተዘጋጅቶና ተጠርዞ ለመረጃነት እንዲቀመጥ የተደረገ ሲሆን፣ ከዋናው መ/ቤት ለ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች የተላኩት ልዩ ልዩ ዕቃዎች በትክክል ለመድረሳቸው ማረጋገጫ እንዲሰጡ በባለሥልጣኑ መ/ቤት በደብዳቤ በተጠየቀው መሠረት ተገቢው ምላሽ ተገኝቷል።

- መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸውና ብልሽት የደረሰባቸው ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ የፎቶኮፒ ማሽኖች፣ መጠረዣ ማሽኖች፣ ጥገና ተደርጎላቸው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ አስችሏል። እንዲሁም ስልክን በሚመለከት ብዛት ያላቸው የቀጥታና የኤክስቴንሽን መስመሮች በብልሽት ምክንያት አገልግሎት አቋርጠው የነበሩትን ከቴሌኮሙኒኬሽን መ/ቤት ጋር በመነጋገርና በግንባርም መ/ቤታቸው በመሄድ ችግሩን በማስረዳት ተሰርተው የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት 16 የስልክ መስመሮች ወደ ዲጂታል ተቀይረው የተሻለ አገልግሎት እየሰጡ ነው።

- በባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች በቀረበው የግዥ መጠየቂያ መሠረት የህትመት መለዋወጫ ዕቃዎች፣ የኤሌክትሪክ

ዕቃዎች፣ የጽሕፈት መሳሪያ፣ የመኪና መለዋወጫ፣ የኮምፒውተር መለዋወጫና የጐማ ግዥ ተፈጽሟል፡፡

- የአዲስ አበባ መስተዳድር የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት የአጥር ሥራና በዋናው መ/ቤት የፍሳሽ ማስወገጃ የውሃ መፍሰሻ ቦይ ሥራ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊውን በመለየት በዕቅዱ መሰረት የአጥሩ ሥራ ተጠናቆ በዋናው መ/ቤት የነበሩ ለሥራው ብቁ ያልሆኑ ተሽከርካሪዎች በቅጥር ግቢው ያለውን ጋራዥ በማጠናከር ተሽከርካሪዎቹ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በዋናው መ/ቤት የ85 ሜትር የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ተሰርቷል፡፡

- ለአሰራር ያመች ዘንድ የመ/ቤቱን የዕቃ ግምጃ ቤት በሁለት የዕቃ ግምጃ ቤት በማደራጀት የየራሳቸው የወጪና የገቢ ሰነድ እንዲኖራቸው ተደርጐ ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የተወሰኑ የመለዋወጫ ዕቃዎች መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ጥገና በሚያካሄድበት በአዲስ አበባ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት ግቢ ጥገና በሚያከናውንበት መጋዘን በማዘጋጀት እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

- በመ/ቤቱ የሚገኙትን አሮጌ ዕቃዎች ለማስወገድ እስካሁን ድረስ የተለያዩ ዕቃዎች ማስታወቂያ ቢወጣም ገዥ አልቀረበም፣ የእንድ ዕቃ የዕቃ ግምት ግን ከአሮጌ ዕቃ አስወጋጅ ኮሚቴ የቀረበው መነሻ ዋጋ ከዕቃው ዝርዝር ጋር ሲነፃፀር ከብር 10 ሺህ በላይ በመሆኑ ጨረታውን በጋዜጣ ለማውጣት ዝግጅቱ ተጠናቆ ለፕሪስ ለመላክ ሁኔታዎች በመመቻቸት ላይ ናቸው፡፡

- የመ/ቤቱ ቢሮዎች በአብዛኛው ቀለም እንዲቀቡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ግድግዳቸው የተላጡ ቢሮዎች የልስን አገልግሎትና የኮርኒስ ቅያሬና የአሸንዳ ሥራዎች ተከናውነው ቢሮዎቹ ደረጃቸውን እንዲጠብቁ ጥረት ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን የየወሩን የዕቃግዥ ሁኔታ በሚመለከት በአይነት በብዛትና የያንዳንዱን ዕቃ ዋጋ የሚገልጽ መረጃ ለመ/ቤቱ የስነ-ምግባር ሞኮንን ሪፖርቱ ተልኳል፡፡ እንዲሁም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማትና ለፌደራል አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤቶች በየሶስት ወሩ የሚቀርቡትን ሪፖርቶች በማዘጋጀት በወቅቱ እንዲደርሳደው ተደርጓል፡፡

### 13.3.2 ትራንስፖርትና ጥገና ዋና ክፍል

- በ1996 በጀት ዓመት በዋናው መ/ቤትና ቅ/ጽ/ቤቶች ለሚገኙ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የተሽከርካሪ ደህንነት መርመራ የተደረገላቸው ሲሆን፤ በተለያዩ ምክንያቶች ለረጂም ጊዜ ቆመው ለነበሩና እንዲሁም አገልግሎት ለሚሰጡ ለሁሉም ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ሰውጥ ተደርጎላቸዋል::

- በዕቅድ ዘመኑ በባለስልጣኑ መ/ቤት ለሚገኙ ተሽከርካሪዎች 341 (አንድ ተሽከርካሪ ከአንድ በላይ ጥገና) በደንበኞች ጋራዥ፣ እንዲሁም 48 ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ጋራዥ ጥገና ተደርጎላቸው ለአገልግሎት ብቁ ሆነዋል::

- በበጀት ዓመቱ በመድን ዋስትና መሸፈን የሚገባቸው 211 ተሽከርካሪዎች የመድህን ሽፋን እንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል::

- በእርጅናና በብልሽት ምክንያት ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆሙ 24 ተሽከርካሪዎች በአንድ ላይ በማሰባሰብ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የሺያጭ የዋጋ ተመን እንዲወሰን ደብዳቤ ተጽፎ ምላሽ እየተጠበቀ ነው::

- በመ/ቤቱ የተቋቋመው ጋራዥ የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ በሰው ሃይልና በማቴሪያል የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል:: በዚሁም መሰረት 12 % ሽፋን ያለው የጥገና ሥራ በዚሁ ጋራዥ ተከናውኗል::

- መ/ቤቱ በገባው ውል መሰረት 36 ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን አገልግሎት ተጠግነው ለሥራ የተሠማሩ ሲሆን፣ 3 ተሽከርካሪዎች በጥገና ላይ ናቸው::

- የመ/ቤቱ የጋራዥ ደንበኞች የጨረታ ጊዜ በመጠናቀቁ እንደገና ህጋዊ በሆነ መንገድ ጨረታ ተካሄዶ ሁለት የመንግስትና አራት የግል ጋራዦች ጨረታውን አሸንፈው ሥራ ጀምረዋል::

- የመ/ቤቱ የነዳጅ አጠቃቀም በሚመለከት በስምንት የተወሰነ ቀን ብቻ ነዳጅ እንዲቀዳና የተሽከርካሪዎችም ኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ እንዲስተካከል ተደርጎ ቁጥጥር እየተደረገ ነው። ተሽከርካሪዎችም በወቅቱ እጥበትና ግሪስ እየተደረገላቸው ነው።

### 13.3.3 የሕትመት ዋና ክፍል

በ1996 በጀት ዓመት በሕትመት ክፍሉ ዉስጥ 257,341 በጥራዝ እንዲሁም 18,981,366 በገጽ የሕትመት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የተለያዩ የሕትመት አገልግሎት ሥራዎች አከናዉኗል።

## 14. በዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

- የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገጽታዎች የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ሰብስቦና አጠናቅሮ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በወቅቱ የማቅረቡ ተግባር የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት ነው። ይህንን መወጣት ይቻል ዘንድ በየዘርፉ የሰለጠነና ልምድ ያካበተ ባለሙያ መኖር ያስፈልጋል። የስታቲስቲክስ ሥራ ብቃት ያላቸውን የቴክኒክ ሰዎችን በተለይም ብቃት ያለው የሜቶዶሎጂ፣ የመረጃ ቅንብር ሥራዎችና ጥልቅ ትንተናና ምርምር የሚሰሩ ባለሙያዎችን ማስማራትን ይጠይቃል። ካለበለዚያ በውጪ አማካሪዎች /ኮንሰልታንቶች/ ላይ ጥገኛ መሆንን ያስከትላል ስለሆነም ባለስልጣን መ/ቤቱ ብቃት ያላቸው በሳል ባለሙያዎችን እንዲይዝ የተሻለ የደመወዝ ስኬል መ/ቤቱ እንዲኖረው ማድረግን ይጠይቃል።

- እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች የሚቀጠሩ ሲሆን፣ ከዚህ በፊትም የተቀጠሩት ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት ከመ/ቤቱ አቅም በላይ እየሆነ መጥቷል። ይህም በመሆኑ በርካታ የሥራ ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶቻቸው ተራርቀው የሚሰሩበት እንዲሁም አንድ ክፍል ከአቅም በላይ የሆነ የሰው ብዛት እንዲይዝ በማድረጋችን ቢሮዎቻችን ለሠራተኞች የተመቹ የሥራ ቦታ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የሠራተኞች የሥራ ተነሣሽነት እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል። በተጨማሪም ከፍተኛ የመንግስት ሃብት የወጣባቸው የተለያዩ የመስክ መገልገያ ዕቃዎች፣

በተለያዩ ጊዜያት መረጃ የተሰበሰበባቸው የጥናት ዶክመንቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች አመች የሆነ ማከማቻ መጋዘን ባለማግኘታቸው ችግሩን የተደራረበ አድርጐታል፡፡ እንዲሁም በመላው አገሪቱ የተከፈቱ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ላይ ተመሣሣይ የሆነ የቢሮና የመጋዘን ችግር ያላባቸው ሲሆን፤ በዓመት መንግሥት ለዋና መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቹ ከግማሽ ሚሊዩን ብር በላይ ለኪራይ ወጪ ያደርጋል በመሆኑም ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቻችን ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እንድንችል ህንጻዎቹ የሚገነቡበት መንገድ በማጥናት ላይ ስለሆንን ጥናቱን በተግባር ለመተርጎም ከመንግስት የበጀት ድጋፍ አስፈላጊ ይሆናል፡፡